# እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2010 በአማራ ብሔራዊ ክልል የነበረዉ የአየር ሁኔታ ግምገማና እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2010 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

## እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2010 የነበረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ግምገማ

ማርች ወር አንዱ የበልግ ወር እንደመሆኑ መጠን በዚህ ወር ዉስጥ በሁሉም የክልላችን ቦታዎች ላይ የተመዘገበዉ የዝቅተኛ የሙቀት መጠን በአማካይ ከ7.5 °c በላይ ነበር፡፡ይህም የሚያመለክተዉ በዚህ ወር ዉስጥ የታየዉ የሌሊቱና የማለዳዉ ቅዝቃዜ የቀነሰበትና በብዙ ቦታዎችም የሌሊቱ ሙቀት (ወበቅ) የጨመረበት መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

አንዳንድ የሰ/ሸዋ፣ የደ/ጎንደር፣የአዊ፣የምዕ/ጎጃም፣የሰ/ወሎና የደ/ወሎ ኪስ ቦታዎች ከ7.5 -10.0 °c የሚደርስ ወርሀዊ አማካይ የዝቅተኛ የሙቀት መጠን ተመዝግቦባቸዋል፡፡ አብዛኛው አዊ ዞን ከፊል የኦሮሚያና የሰ/ጎንደር ዞን ፣ለኦሮሚያ ዞን አዋሳኝ የሆኑ የደቡብ ወሎ ዞን ቦታዎች፣ እንዲሁም ጥቂት የሰሜን ወሎ የምስራቅና የምዕራብ ጎጃም ዞን ቦታዎች ከ12.5 - 15 °c የሚደርስ ወርሀዊ አማካይ የዝቅተኛ የሙቀት መጠን ታይቶባቸዋል፡፡ ጥቂት የሰ/ጎንደር ዞን ቦታዎች ከ15 - 17.5 በ °c ሲመዘግቡ አንዳንድ የሰ/ጎንደር ዞን ኪስ ቦታዎች ከ17.5 - 22 °c የሚደርስ ወርሀዊ አማካይ የዝቅተኛ የሙቀት መጠን ተመዝግቦባቸዋል፡፡ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ የሚገኙትና አብዛኛውን የክልላችን ክፍል የሚሸፍነው ከ10 - 12.5 °c የሚደርስ ወርሀዊ አማካይ የዝቅተኛ የሙቀት መጠን ተንፀባርቆባቸዋል፡፡ በዚህ ወር ከሌሎች ጣቢያዎች አንፃር ሲታይ የሌሊቱና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ከፍ ያለባቸዉ የክልሉ ቦታዎች ዉስጥ ለአብነት ያህል ወ/ጤና 8.0፤ ዳንግላ 8.4 እንዲሁም ደ/ታቦር 8.8 በ °c በአማካይ ይጠቀሳሉ (ካርታ1ን ይመልከቱ)፡፡

## እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2010 የነበረው ከፍተኛ የሙቀት መጠን ግምገማ

በማርች ወር ዉስጥ በአማራ ክልል የታየዉ ወርሃዊ የከፍተኛ የሙቀት መጠን ግምገማ እንደሚያሳየዉ ሰ/ሸዋ ና አብዛኛውደ/ወሎ፣ ለደ/ወሎ አዋሳኝ የሆኑ የሰ/ወሎ ዞን ቦታዎች፣ ለሰ/ሸዋ ዞን አዋሳኝ የሆኑት የኦሮምያ ዞን ቦታዎች እንዲሁም አንዳንድ የደ/ጎንደር ዞን ኪስ ቦታዎች ከ20 - 25 $^{o}$c የሚደርስ ወርሀዊ አማካይ የከፍተኛ የሙቀት መጠን ተመዝግቦባቸዋል::አብዛኛው አዊ ዞን፣ከፊል የሰ/ጎንደርና ምዕ/ጎጃም ዞን ቦታዎች እንዲሁም ለምዕ/ጎጃም ዞን አጎራባች የሆኑ የምስራቅ ጎጃም ዞን ኪስ ቦታዎች ከ30 - 35 $^{o}$c የሚደርስ ወርሀዊ አማካይ የከፍተኛ የሙቀት መጠን ተመዝግቦባቸዋል:: አንዳንድ የሰ/ጎንደር ኪስ ቦታዎች ከ35 - 40 $^{o}$c የሚደርስ ወርሀዊ አማካይ የከፍተኛ የሙቀት መጠን ተንፀባርቆባቸዋል:: ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ የሚገኙት አብዛኛው የክልላችንን ክፍል የሚሸፍኑት ቦታዎች ከ25 - 30 በ$^{o}$c የሚደርስ ወርሀዊ አማካይ የከፍተኛ የሙቀት መጠን ተመዝግቦባቸዋል:: በማርች ወር ዉስጥ ከፍተኛዉን የከፍተኛ የቀን የሙቀት መጠን ከመዘገቡ ጣቢያዎቻችን መካከል ለመጥቀስ ያህል መተማ 39.6 ፣ቻግኒ 33.4 እና ላይበር 32.6 በ $^{o}$c በአማካይ ይጠቀሳሉ (ካርታ2ን ይመልከቱ)::

## እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2010 የነበረው የዝናብ መጠን ግምገማ

ምዕራብ አማራ እና ለምዕራብ አማራ አጎራባች የሆኑት የምስራቅ አማራ ስፍራዎች፣ከፊል ሰ/ወሎ ፣ አንዳንድ የደ/ወሎና የሰ/ሸዋ ዞን ኪስ ቦታዎች ከ50 ሚ.ሜ በታች የሆነ ወርሀዊ የዝናብ መጠን ተስተውሎባቸዋል:: አብዛኛው ሰ/ሸዋ፣አብዛኛው ደ/ወሎ፣ዋቂት የሰ/ወሎ ዞን ቦታዎች ከ50 - 75 ሚ.ሜ የሚደርስ ወርሀዊ የዝናብ መጠን ተመዝግቦባቸዋል:: ኦሮምያ ዞን፣የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች ምስራቃዊ ክፍል እንዲሁም አንዳንድ የሰ/ሸዋ ዞን ኪስ ቦታዎች ከ75 - 160 ሚ.ሜ የሚደርስ ወርሀዊ የዝናብ መጠን ተመዝግቦባቸዋል:: በማርች ወር ዉስጥ የተሻለ ዝናብ ከታየባቸዉ ጣቢያዎቻችን ዉስጥ ለአብነትያህል በባቲ 158.8 በጨፋ 131.6 እንዲሁም በሲሪንቃ 91.1 በሚሜ የሆነ ዝናብ የመዘገቡ ለአብነት የሚጠቀሱ ጣቢያዎቻችን ናቸዉ(ካርታ3ን ይመልከቱ)::

የዝናብ ስርጭቱ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር አብዛኛው ምስራቅ አማራ፣አብዛኛው ደ/ጎንደር፣ከፊል የሰ/ጎንደርና የምስ/ጎጃም ዞን ቦታዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት ተስተውሎባቸዋል፡፡የአዊ ዞንና የምዕ/ጎጃም ዞን ቦታዎች፣ከፊል ምስ/ጎጃም፣አንዳንድ የደ/ጎንደር የሰሜንና የደቡብ ወሎ እንዲሁም የሰ/ሸዋ ኪስ ቦታዎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ ስርጭት ተንፀባርቆባቸዋል (ካርታ 4ን ይመልከቱ)፡፡

## የአየር ሁኔታ ለወባ መራባትና ስርጭት ያለው ተፅዕኖ

የግሮቬር ኮፔክ(Grover Kopec et al 2006) ምርምርና ጥናት እንደሚያሳየው በአፍሪካ ሀገሮች ለወባ መራባትና መተላለፍ ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው:-

1. በወሩ ውስጥ የጣለው የዝናብ መጠን ከ80 ሚ.ሜ በላይ ሲሆን
2. የወሩ አማካይ የሙቀት መጠን ከ18 - 32 $^{o}$c ሲሆን እና
3. የወሩ አማካይ የእርጥበት ደረጃ ከ60 % በላይ ሲሆን ነው፡፡

ይህንን ጥናት መሰረት በማድረግ በክልላችን ውስጥ ለሚገኙ 10 ጣቢያዎች በማርች ወር ለወባ መራባትና ስርጭት አመች የአየር ሁኔታ መኖር ወይም አለመኖሩን የሚያሳይ ሰንጠረዥ እንደ ሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 1. በክልላችን በተመረጡ ጣቢያዎች ላይ በማርች ወር 2010 ወባ የመፈጠር ዕድሉን የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የጣቢያው ስም | የአየር ሁኔታ | | | ወባ የመፈጠር ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሙቀት($^{0}$c) (TT) | ዝናብ(mm) (RF) | የእርጥበት ደረጃ(%) (RH) | |
| 1 | ባቲ | 19.9 | 158.8 | 70 | አለ |
| 2 | ጨፋ | 20.8 | 131.6 | 68 | አለ |
| 3 | ኮምቦልቻ | 19.9 | 70.7 | 59 | የለም |
| 4 | ሲሪንቃ | 18.9 | 91.1 | 66 | አለ |
| 5 | እንዋሪ | 16.6 | 85.1 | 54 | የለም |
| 6 | ደ/ማርቆስ | 19.3 | 42.9 | 33 | የለም |

*አንዳንድ ከአየር ንብረት ሁኔታ ውጭ የሆኑ ነገሮች ለወባ መራባትና መተላለፍ የበኩላቸውን ድርሻ ስለሚያበረክቱ የወባ ስርጭቱን ለመቆጣጠር ከላይ ከተጠቀሰው መረጃ በተጨማሪ ከእሳቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው እንላለን፡፡*

## እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2010 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከማርች1-31/2010 በክልላችን የነበረውን የአየር ሁኔታ እና በግብርናው ዘርፍ ላይ የነበረውን ተፅዕኖ ስንመለከት በክልሉ ምዕራባዊ ቦታዎች ደረቅ (dry) እና በጣም ደረቅ (very dry) የሆነ የአፈር እርጥበት የነበረው ሲሆን ነገር ግን በምስራቁና በአብዛኛው በልግ ተጠቃሚ በሆነው የክልሉ ክፍል ከመካከለኛ ደረቅ (moderately dry) እስከ እርጥብ (Humid) የሆነ የአፈር እርጥበት ነበረው፡፡ ይህም በልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ለተዘሩ አዝዕርቶች የተመቻቸ ሁኔታን ፈጥሮአል፡፡ ለዚህ የአፈር እርጥበት መኖር በዋነኛነት አስተዋጽኦ ካደረጉት የሚቲዎሮሎጂካል ሁኔታዎች በምስራቁ የክልሉ ክፍል በወሩ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ በመዝነቡ ነው (Table:1 ን ይመልከቱ)፡፡

በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበሩትን የአፈር እርጥበት ሁኔታዎች ለማየት ያህል በምስረቁ የክልላችን ቦታዎች በላሊበላ ደረቅ(dry) የአፈር እርጥበት ከመኖሩ ውጭ በቀሪዎቹ በምስራቁ የክልላችን ቦታዎች ላይ  መካከለኛ ደረቅ(moderately dry)፣ እርጥበት አዘል (moist) እና እርጥብ (Humid) ነበሩ፡፡ በምእራባዊ የክልሉ ቦታዎች የትነት መጠኑ በአንጻራዊነት በምስራቅ አማራ ካለው የበለጠ ነበር፡፡ በአጠቃላይ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በወሩ የነበረው የአየር ሁኔታ በተለይም ለበልግ አብቃይ ቦታዎች የተመቻቸ ጊዜን ፈጥሮ አልፎአል (ካርታ 0 ን ይመልከቱ)፡፡

*Table1: AGRO-CLIMATIC ELEMENTS FOR THE MONTH OF MARCH /2010*

| STATION | ETo (mm/day) | ETo (mm/month) | Moisture Status | Remark |
|---|---|---|---|---|
| ***Bahirdar*** | 4.07 | 122.1 | 0.0 | VD |
| ***Chagini*** | 4.4 | 132 | 0.0 | VD |
| ***D/Markos*** | 4.4 | 130.5 | 0.3 | MD |
| ***D/Tabor*** | 3.7 | 111 | 0.3 | MD |
| ***Dangla*** | 3.7 | 111 | 0.0 | VD |
| ***Gondar*** | 4.6 | 137.7 | 0.2 | D |
| ***Motta*** | 4.2 | 125.7 | 0.2 | D |
| ***Pawe*** | 3.9 | 116.4 | 0.0 | VD |
| ***Bullen*** | 3.6 | 108.3 | 0.0 | VD |
| **Layber** | 3.94 | 118.2 | 0.0 | VD |
| ***Bati*** | 2.82 | 84.6 | 1.9 | H |
| ***Cheffa*** | 3.7 | 110.4 | 1.2 | H |
| ***Combolcha*** | 2.9 | 86.1 | 0.8 | M |
| ***Lalibela*** | 3.7 | 112.2 | 0.2 | D |
| ***Sirinka*** | 3.4 | 100.5 | 0.9 | M |
| ***Wegeltena*** | 3.5 | 105.3 | 0.4 | MD |
| ***Wereilu*** | 3.3 | 99.3 | 0.4 | MD |
| ***D/birhan*** | 3.6 | 107.7 | 0.4 | MD |
| ***Enewary*** | 3.5 | 104.1 | 0.8 | M |

Note

VD---------------Very Dry (for moisture status Less than 0.1)
D---------------Moderately Dry (for moisture status between 0.1 and 0.25)
MD-----------------Dry (for moisture status between 0.25 and 0. 5)
M----------------Moist (for moisture status between 0. 5 and 1.0)
H-----------------Humid (for moisture status greater than 1.0)
ETo-----------Reference Crop Evapotranspiration in millimeters per day

## እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-30/2010 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

የበልግ ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ የክልላችንን የበልግ አብቃይ አካባቢዎች በስፋት የሚያዳርሰው በኤፕሪል ነው። ስለሆነም በኤፕሪል የሚጥለው ዝናብ በመደበኛው ሁኔታ በበልግ ወቅት ከሚጠበቀው የዝናብ መጠንና ስርጭት ጋር ሲወዳደር ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። የበልግ ወቅት ዋነኛ የዝናብ ጊዜያቸው በሆኑት በክልላችን ምሥራቃዊ አካባቢዎች በወሩ የሚጥለው ዝናብ ከቀሪዎቹ የበልግ ወራት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነው።

በመጪው ኤፕሪል ለሚኖረው ዝናብ የአየር ሁኔታ ገፅታዎች ምቹ እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ስለሆነም በብዙ የክልላችን ክፍሎች ላይ ከመደበኛው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ዝናብ እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚኖረው ዝናብ አንፃራዊ ጥንካሬ እንደሚኖረው ይጠበቃል።

በአጠቃላይ ምሥራቅ አማራ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፣ የምዕራብ አማራ አካባቢዎች ከመደበኛው ጋር የሚቀራረብ ዝናብ የሚኖራቸው ቢሆንም አንዳንድ ቦታዎች በአብዛኛው ከመደበኛው ያነሰ ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ።

☎ 058 220 77 86 058 220 77 92 ✉ 219 e-mail:- **b-darmet@ethionet.et** BahirDar/ባህር ዳር